የሰ/መ/ቁ. 52525

ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ የትምወርቅ ሰብስቤ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ሸዋረጋ ደመቀ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የአመልካች የክስ ምክንያት ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠበት ነው በማለት የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ለመሆኑ ለመመርመር ነው፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር የእርሻ መሬት ይዞታን የሚመለከት ነው፡፡ ከሳሽ አመልካች ሆና ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ ተጠሪ ያለአግባብ የያዘውን የእርሻ መሬት እንዲለቅልኝ ስትል አመልካች በሸርካ ወረዳ ፍ/ቤት ክስ ያቀረበች ሲሆን ተጠሪ በተመሳሳይ ጉዳይ በመ/ቁ. 345/97 በ14/6/2001 ዓ.ም ውሳኔ ተሰጥቷል ሲል መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን የወረዳው ፍ/ቤት ቀደም ሲል በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ ያልተሰጠ እና ይልቁንም ከሳሽ ማስረጃ አሟልታ ክስ እንድታቀርብ መብት ተጠብቆላት መዝገቡ የተዘጋ መሆኑን ጠቅሶ መቃወሚያውን ውድቅ ማድረጉን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪውን መሬት ለአመልካች እንዲለቅ ወስኗል፡፡ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ አጽንቷል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኂላ በጉዳዩ ላይ ቀደም ሲል ውሳኔ ተሰጥቶበታል ይህ ከሆነ ደግሞ በድጋሚ ሊታይ አይገባም (res judicata) በሚል የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ ተጠሪም በሰጠው መልስ ቀድሞ ለአመልካች የተጠበቀ መብት የለም መዝገቡ በውሳኔ ተዘግቷል በማለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡

እኛም ከፍ ሲል ከተመለከተው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ የሻረው ጉዳዩ ቀድሞ ውሳኔ ያገኘ ነው በሚል ምክንያት መሆኑን ከውሳኔው ተረድተናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ይዘት መረዳት የቻልነው አመልካች ቀደም ሲል ያቀረበችው ክስ በፍርድ ቤቱ ከተሰማ በኂላ የአመልካች ክስ ግልጽነት የሚጐድለውና ማስረጃም ያልተሟላ በመሆኑ ማስረጃዋን አሟልታ ክስ እንድታቀርብ መብት ተጠብቆላት መዝገቡ የተዘጋ ስለመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በፍሬ ጉዳዩ ላይ የተሰጠ ውሳኔ አለ ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ ሙሉ በሙሉ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ፍርድ አልሰጠም፡፡ ይልቁንም ማስረጃ አሟልተሽ ማቅረብ ትችያለሽ የሚል ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ይህ አካሄድ በመርህ ደረጃ አግባብነት ያለው ነው ባይሰኝም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 91/4/ በተደነገገው አግባብ ለጉዳዩ ፍትሐዊ ውሳኔ አሰጣጥ ይበጃል ብሎ ካመነ ፍ/ቤቱ ማሻሻያ እንዲደረግ ማዘዝ ይችላል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከዚህ ይልቅ አመልካች ማስረጃ አሟልታ ክስ እንድታቀርብ በማድረጉ ይህ ውሳኔው ሥነ-ሥርአታዊ አይደለም የሚለው ወገን በይግባኝ አስካላሻረ ጊዜ ድረስ ውሳኔውን መሰረት በማድረግ አዲስ ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም ሊባል አይገባም፡፡

ከዚህ ሌላ የቀድሞ መዝገብ ላይ በፍሬ ጉዳይ ረገድ የተሰጠ ውሳኔ ስለመኖሩ አልተጠቀሰም፡፡ እንግዲህ የጉዳዩ አጠቃላይ ይዘት ይህንን የመሰለ መሆኑን ከተገነዘብን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ መሰረት የሚሸፈን ነውን? የሚለውን እንመለከታለን፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ መሰረት በማድረግ ድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይቻለው በቀድሚው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑ የተከራካሪ ወገኖች አንድነት ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑም መረጋገጥ አለበት፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቀደም ሲል በተጠሪ ላይ ያቀረበችው ክስ በተመሳሳይ ፍሬ ነገር ላይ ቢሆንም በቀድሞ መዝገብ በፍሬ ነገር ረገድ የመጨረሻ ውሳኔ እንዳልተሰጠበት ይልቁንም አመልካች ክሷን በማስረጃ አሟልታ እንድታቀርብ መብት የተጠበቀላት መሆኑን ከፍ ሲል ተመልክተናል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ላይ በቀዳሚው መዝገብ  የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ይህ መለያ እስካልተሟላ ድረስ ደግሞ አመልካች ያቀረበችው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ ሥር የሚሸፈን አይሆንም፡፡ ስለዚህም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በድጋሚ የቀረበ ነው (res judicata) በሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 5/1/ ይሸፈናል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ውሳኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በሌላ በኩል አከራካሪው መሬት የማን ነው የሚለውን በተመለከተም ማስረጃ በማጣራት የወረዳው  እና ከፍተኛው ፍ/ቤት የተሻለ ማስረጃ የአመልካች መሆኑን ስለማረጋገጣቸው ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ስለሆነም በፍሬ ነገር ረገድ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ማስረጃ መሰረት ያደረገ መሆኑን ስለተገነዘብን ባለበት ሊፀና የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 88224 በ17/05/2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሸርካ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06008 በ4/7/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19080 በ24/11/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ